**ሰሞነኛው የሴራ ፖለቲካ...**

የሴራ ፖለቲካ እና የበሬ ወለደ ትርክት ለኢትዮጵያ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ በዚህ ሰሞንም አንድ "ጥብስ" የሆነ የሴራ ፖለቲካ እየሰማን ነው፡፡ እሱም በኦሮሚያ እና በሱማሌ ክልሎች ወሰን አካባቢ ግጭት ተከስቶ እጅጉን በሚያሳዝን እና በሚያበሳጭ ሁኔታ በሰው ህይወት፣ በአካል እና በንብረት ላይ ጉዳት መድረሱን እንዲሁም በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች መፈናቀላቸውን ተከትሎ የችግሩ ምንጭ ወደ ሌላ ሩቅ ያለ አካል ለማላከክ እና የጥላቻ ፖለቲካን ለማራመድ እየተደረገ ያለ ጥረት ነው፡፡ መሰል ችግሮች በተከሰቱ ቁጥር በህዝቦች መካከል ጥርጣሬ በመፍጠር ሁከቶች እንዲበራከቱ እና ልማቱ ተንገራግጮ እንዲቆም የሚቋምጡ ሀይሎች በእንደዚህ ዓይነት የከሰረ ፖለቲካ ውስጥ የመሰማራታቸው ጉዳይ ቁርስ እና ምሳ የመብላት ያህል የተለመዱ እየሆኑ መጥቷል፡፡ መልስ እና ማብራሪያ በመስጠቱ በኩል የመንግስት የኮሚኒኬሽን አውታሮች የሚያሳዩት ቸልተኝነትም ችግሩ እንዲቀጥል አስተዋፅኦ ሳያደርግ አልቀረም፡፡

የሴራ ፖለቲካ አራማጆች ዋነኛ ዒላማ ለአገሩ ቀና አሳቢ የሆነ ማንኛውም ዜጋ፣ አመራር ወይም ተቋም ሊሆን እንደሚችል በተደጋጋሚ አሳይተውናል፡፡ በእውነተኛ አብዮታውያኑ ሀይሎች እና አመራሮቻቸው እንዲሁም መስመሩን ይደግፋል ተብሎ የሚታሰበውን የህብረተሰብ ክፍል ላይ ለመሰንዘር የሚሞከረው ጥቃት እና የሚናፈሰው አሉባልታ ግን በመጠንም በዓይነትም ሲመዘን ሪከርድ የሚመዘግብ አካል ቢኖር ብዙ ሪከርዶችን እንደሚሰብር ጥርጥር የለውም፡፡ የሴራ ፖለቲካ አራማጁ ሀይል በሚነዛው ውዥንብር ምክንያት ህዝቦች ቢቃቃሩ፣ ወደ ግጭት ቢገቡ ወይም የአገር አንድነት ቢናጋ ምኑም አይደለም፡፡ ከዚህም በመነሳት ነው ህዝብ እንደ ህዝብ ጭምር እንደ ጠላት ከመፈረጅ ወደ ኋላ የማይለው፡፡ እንግዲህ ይህ ተግባርም ፖለቲካ ተብሎ ሊጠራ ነው!

እነዚህ ሀይሎች እንደ ልማዳቸው በኦሮሚያ እና በሱማሌ ክልል አዋሳኝ አካባቢዎች ለተፈጠረው አሳዛኝ ግጭት አንዳንድ የኢህአዴግ ነባር አመራሮች አለፍ ሲልም አንዳንድ የኢህአዴግ አባል ብሔራዊ ድርጅቶች ዋና ተጠያቂ ለማድረግ እየተውተረተሩ ነው፡፡ እስኪ ቆም ብለን ለማሰብ እንሞክር ጎበዝ... ምን ለማግኘት ሲባል ነው እነዚህ ነባር አመራሮች ወይም አንዳንድ ለምሳሌ እንደ ህወሓት ያሉ የግንባሩ አባል ድርጅቶች እንደዚህ ዓይነት ዘግናኝ ግጭት እንዲከሰት የሚሰሩት? የእነዚህ ድርጅቶች ወይም ነባር አመራሮቻቸው ፖለቲካዊ ስብእና እና ታሪክስ በእንደዚህ ዓይነት ተግባር ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ ያመላክታል ወይስ እንዲገቡ ይፈቅዳል? ይሁንና እንዴትስ ነው ይሄንን ማከናወን የሚችሉት ለዛም በስውር መንገድ፤ ሰው ሳያያቸው? ነገሩን ለመመርመር ያህል ጥያቄዎችን አነሳን እንጂ የሴራ ፖለቲካ አራማጆች የበሬ ወለደ ፖለቲካ ለማራመድ ምንም ዓይነት ተጨባጭ ማስረጃ ወይም አሳማኝ ትንታኔ ማቅረብ "አያስፈልጋቸውም"፤ በሐሰት መወንጀል ብቻ ዓላማቸውን የሚያሳካ ስለሚመስላቸው! ዳሩ ግን ምንም እንኳን በስተመጨረሻ ሁሌ ተሸናፊነታቸው የማይቀር ቢሆንም የእነዚህ ሀይሎች አሉባልታ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን የሰላም፣ የልማት እና የአገር ግንባታ ስራዎች ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ አስተዋፅኦ ማድረጉ አልቀረም፡፡

የሳምንታችን የሴራ ፖለቲካ አራማጆች ካሰሙን ትንግርቶች መካከል ነባሮቹን (እነማን እንደሆኑ በስም ተዘርዝረው ባንሰማም) የኦህዴድ አመራሮች ቀንደኛ የሁከቱ ቀስቃሽ እንደሆኑ እና ይሄንን "ራዕያቸው" እንዲሳካ ደግሞ የሌሎች አብዮታዊ ድርጅቶች ነባር አመራሮች እንዲሁም የሱማሌ ክልል አመራሮች ሁነኛ አጋር እንደሆኑዋቸው የሚያትተውን ይገኝበታል፡፡ እውነት ግን እንኳንስ በተደራጀ መንገድ ከኦህዴድ ነባር አመራሮች መካከል የተወሰኑ ግለሰቦች እንኳን እንደዚህ ዓይነት ዘግናኝ ግጭት

እንዲፈጠር ይመኛሉ፤ ከምኞት አልፈውም በተግባር እንዲከሰት ይሰራሉ፤ ብሎ ማሰብ አይሰቀጥጥም? ነባሮቹ የኦህዴድ አመራሮች (ብዙዎቹ የአሁኑ አመራሮችም ጨምሮ) እኮ ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ሲባል ለህወይታቸው ሳይሳሱ በለጋ ዕድሜያቸው የደርግን ስርዓት ለመደምሰስ ትግል ያካሄዱ፣ ከዛ በኋላም ከህዝቡ ጋር በመሆን ብዙ የደከሙ እና በፈታኝ ወቅቶች እንኳን ህዝባዊነታቸውን ያስመሰከሩ ናቸው፡፡ ምን ዓይነት ተአምር ቢፈጠር ነው ዛሬ ላይ ደርሰው በእንደዚህ ዓይነት አስነዋሪ ተግባር የሚሰማሩት? ምንስ ለማግኘት?

አረ ለመሆኑ እነዚህ ነባር የተባሉ አመራሮች እንደዚህ ዓይነት ፍላጎት ቢኖራቸውም እንኳን በየትኛው መዋቅር፤ በየትኛው የእዝ ሰንሰለት፤ በየትኛው እነሱ የሚያዙበት መንግስታዊ ሀብት ነው እንደዚህ ዓይነቱን ግጭት መምራት የሚችሉት? በምን ዓይነት አስማት ይሆን በወሰን አከባቢ ያለውን ህዝብ አሳምነውና መርተው ወደ ግጭት የሚያስገቡት? ህዝቡን ሌት ተቀን የማግኘት እና የማስተዳደር እድል ያለው አሁን ያለውን አመራር እንደሆነ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም፡፡ ሲጀመር ነባር፣ አዲስ የሚል የአመራር ክፍፍል ለዛም በእንደዚህ ዓይነት የልዩነት ደረጃ አለ እንዴ? አዲስ የተባለው አመራር ነባር ከተባለው አመራር መሰረታዊ ልዩነት እንዳለው የሚያሳይ የፖለቲካ ፕሮግራም አለ እንዴ? ነባሩም አዲሱም ተመሳሳይ ድርጅትና መንግስት አይደለም ወይ የሚመሩት? ነባሩ አመራር አይደለም ወይ አዲሱን አመራር የገነባ፤ አገርን የመምራት ሐላፊነት ያስረከበው? መልሱ ለአንባቢው ልተወው፡፡ በእንደዚህ ዓይነት መጠን ህዝቦችን ወደ ግጭት የመምራት ዓቅም የፈጠረ የነባር አመራር ቡድን አለ ብለን ከተቀበልን ነባሩ አመራር ከአዲሱ አመራር ይልቅ ህዝቡን የማግኘት፣ የመቀስቀስ፣ የመምራት እንዲሁም ከሌሎች ጋር ሆኖ የመስራት ዓቅም ገንብቷል ማለታችን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ፍፁም ሊታመን የማይችል ነገር ነው፡፡

የሴራ ፖለቲካ አራማጁ ሀይል ህወሓትን አልያም የመከላከያ ሀይልን ተጠቅመው ነው ወዘተ. እያለ ሊያደነቁረን ሞክሯል፡፡ ካሁን ቀደምም የአማራ መሬት የነበረን የወለጋ መሬት ህወሓት ለኦሮሞ አሳልፎ ሰጥቶታል በማለት በሶስቱም ህዝቦች መካከል ውጥረትና ጥላቻ እንዲፈጠር የሚያደርግ የጥፋት ስብከት ለመስበክ ዘምቷል፡፡ ህወሓት በእንደዚህ ዓይነት ርካሽ ተግባር ውስጥ እንዲሰማራ የሚያስችለው ስብእና እና ታሪክ አለውን? የህወሓት ድርጅታዊ ስብእና ተበላሸ ብለን እናስብና ምን ትርፍ ለማግኘት ሲል ነው ግጭት እንዲፈጠር፣ ሰው እንዲሞት፣ አካሉ እንዲጎድል እና ከቀዬው እንዲፈናቀል የሚሰራው? የሴራ ፖለቲከኞች ዘንግተውት ከሆነ አንድ ጥሬ ሀቅ እናስታውሳቸው፤ ህወሓት እኮ ለመላ ኢትዮጵያውያን ነፃነት ሲባል ህዝብን ከጎኑ በማሰለፍ ከሚገባው በላይ መስዋእትነት የከፈለ ድርጅት ነው፡፡ ህወሓት እኮ መላ ዲሞክራሲያውያን ሀይሎች ወደ አንድ ጠረጴዛ እንዲመጡ፤ የድህረ-ደርግ ኢትዮጵያ በጠንካራ መሰረት ላይ እንድትገነባ፣ ሁሉም ህዝቦች በእኩልነት፣ በመከባበርና በመፈቃቀድ አገራቸውን እንዲያለሙ እና ኑሮዋቸውን እንዲያሻሽሉ ከማንም የላቀ (እደግመዋለሁ ከማንም የላቀ) አስተዋፅኦ ያደረገ ድርጅት ነው፡፡ የሴራ ፖለቲከኞች ይህም እንዳልነበረ ወይም ገልብጠው ሊነግሩን ቢቃጣቸው የሚደንቅ አይደለም፡፡ ታዲያ በምን አመክንዮ ነው አሁን ላይ ደርሶ ወንድም/እህት ህዝቦች እርስ በራሳቸው እንዲናከሱ ፊታውራሪ የሚሆነው? ህወሓት መወቀስ ባለበት ሌላ ጉዳይ (ለምሳሌ በሚያስተዳድረው ክልል እና በፌደራል መንግስቱ ባለው ድርሻ መጠን መልካም አስተዳደር ህዝቡን በሚያረካ ደረጃ ባለማስፈኑ) ይወቀሳል እንጂ ህዝቦች እንዲጋጩ ሆን ብሎ ሰራ ብሎ ማለት የእብደት ጫፍ ነው፡፡ ህወሓትን የሚያውቁ ሁሉ ህዝቦች እንዲጋጩ የሚተጉ ሀይሎችን እንዴት እንደሚጠየፍ እና በርትቶ እንደሚታገላቸው ይገነዘባሉ፡፡

የሴራ ፖለቲከኞቹ ነባሮቹ የኦህዴድ አመራሮች እዛ አከባቢ ያለውን የመከላከያ ሀይል በመጠቀም ነው ግጭቱን የሚያካሂዱት ሲሉም ሰምተናል፡፡ መከላከያን የሚያዘው የፌደራል መንግስት ወይስ ነባሮቹን የኦህዴድ ወይም የሌላ ድርጅት አመራሮች? ወይስ ህወሓት? አሉባልተኞቹ አይ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ታጋይ ጀነራሎች በመጠቀም ነው ሲሉም አድምጠናል፡፡ አረ በህገ አምላክ! የመከላከያ ሀይላችን በታጋይ የትግራይ ተወላጅ ጀነራሎች ብቻ የተገነባ እንዳልሆነ እኮ ግልፅ ነው፡፡ መከላከያ ሀይሉ ጥቂቶች የሚፈነጩበት ተቋም ቢሆን ኖሮ አሁን የደረሰበትን ደረጃ ከቶውንም አይደርስም ነበር፡፡ በነገራችን ላይ ይሄኛው አሉባልታ ነባር ታጋዮቹ ምናልባት ከሁላችንም በበለጠ የህዝብ ስቃይ ምን ማለት እንደሆነ እንደሚገነዘቡ እና ዕድሜ ልካቸው ያን ሲያወግዙ እና ሲታገሉ እንዳሳለፉም የዘነጋ ነው፡፡ ግልፅ መሆን ያለበት ነገር እንኳንስ ህብረ ብሄር ሆኖ ሙሉ በሙሉ የአንድ አካባቢ ተወላጆች ብቻ ያሉበት አሀድ ቢሆንም እንኳ የመከላከያ ሀይላችን በእንደዚህ ዓይነት ዝቃጭ ተግባር እንደማይሳተፍ በየሄደበት ሁሉ በተግባር አስመስክሯል፡፡ ብሄሩ ከዚህም ይሁን ከዛ ምንም ለውጥ አያመጣም፡፡ ዋናው ህዝባዊነቱ እና ዓላማውን የሚያውቅ ሀይል መሆኑ ነው፡፡

የሴራ ፖለቲካው የሱማሌ ክልል መንግስት፣ የክልሉ ገዢ ፓርቲ እና ልዩ ሀይል ደግሞ ለነባሮቹ አመራሮች እና ለመከላከያ በመሳሪያነት እንዳገለገሉ ይከሳል፡፡ እንዴት ሆኖ? የሱማሌ ክልል መንግስት እና አመራሮች እንዴት ብንገምታቸው ነው የሌላውን የጥፋት ሴራ ተግባሪ ለመሆን ዘው ብለው ግጭት ውስጥ ይገባሉ ተብሎ የሚታሰበው? ለዛም ከ1400 ኪ.ሜ. በላይ ከሚያዋስናቸው እና አብረውት ለዘላለም ከሚኖር ጎረቤት ብቻ ሳይሆን ከተዋለዱበት ህዝብ እና ክልል ጋር! እንደዚህ ዓይነቱ አሉባልታ የሱማሌ ክልል መንግስት ወይም አመራር ዜጎችህን ለእሳት ስጥ ሲባል የሚሰጥ፣ ሂድ ሌላውን ወንድም ህዝብ ጨፍጭፍ ሲባል የሚጨፈጭፍ አድርጎ የሚሰብክ እጅጉን የዘቀጠ የዘመኑ "ታላቅ!" ሴራ ነው፡፡ የሱማሌ ክልል መንግስት ወይም አመራር ምን መና እንዲዘንብለት ነው የጥቂት ሰዎች እኩይ ዓላማ አስፈፃሚ የሚሆነው? ወይንስ የክልሉ መንግስት እና ፓርቲ ጥቅሙን ለይቶ አይረዳም ማለት ነው? ግጭት ሁሉም ህዝቦች ልክ እንደማናችንም ጥቅማቸው ሲነካ ወይም የተነካ ሲመስላቸው ወይም ኢፍትሀዊ የመሰላቸው ጉዳይ ሲኖር ብቻ እና ሌላ መፍትሔ በወቅቱ ሲያጡ የሚገቡበት አማራጭ እንደሆነ መረዳቱ የፖለቲካ ሀ...ሁ... ነው፡፡

የሴራ ፖለቲካ አራማጆቹ እና በእነሱ አስተሳሰብ የተመሰጡ አንዳንድ ቅን ወገኖቻችን ግጭቱ የተፈጠረው "አዲሱን" የኦህዴድ አመራር "ጥርስ ስለተነከሰበት" እና አመራሩን ለመቅጣት በማለም ሆን ተብሎ እንደተፈጠረ ሊነግሩን ሞክሯል፡፡ ሲጀመር ለምን ይቀጣል? ምን ስለአጠፋ? ኦህዴድ እና ሌሎቹ አብዮታዊ ሀይሎች እኮ በአንድ የፖለቲካ ፕሮግራም ስር የሚታገሉ ሀይሎች ናቸው፡፡ ልዩነት፣ ጉድለት ወይም ሌላ ችግር ቢያጋጥምም እንኳን እየተተጋገሉ እና እየተራረሙ መራመድን የተካኑ ሀይሎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በህወሓት እና ብአዴን መካከል አለመግባባቶች ተከስተው እንደነበር እና ጠንከር ያለ ትግል ተካሂዶ ነገሮች ፈር መያዛቸውን ማንም የሚያውቀው ሀቅ ነው፡፡ ለኦህዴድ ሲሆን አብዮታውያኑ ሀይሎች የተለየ አካሄድ (ለዛም ህዝቦችን ወደ ግጭት የሚያስገባ) የሚከተሉበት ምንም ዓይነት አመክንዮ ወይም ተጨባጭ ጥቅም የለም፡፡

የሴራ ፖለቲካ አራማጁ ሀይል (በጥበት ወይም በትምክህት ምክንያት ከአፍንጫው አርቆ ማየት የተሳነው ሁሉ) ለዘላለም ተሸክሞት የሚኖር ድክመቱ አብዮታውያኑ እንደ ህወሓት ያሉ ድርጅቶች እንደ ራሱ የሚያስቡ እና እንደራሱ ወደ ዘቀጠ የፖለቲካ ቁማር የሚገቡ ሀይሎች የሚመስለው መሆኑ ነው፡፡ አረ ተማሩ! አልገባ ብሏቸው ነው እንጂ በወሰን አካባቢ ያለውን

ህዝብ ማጋጨት እኮ "ጥርስ የሚነከስበት" ሀይል በኦሮሚያም ይሁን በሱማሌ ክልሎች ወደ ስልጣን እንዲመጣ ከመጣም እንዲጎመራ የሚያደርግ ዕድል የሚከፍት ብሎም አገሪቷን የመበታተን አደጋ እንዲጋረጥባት የሚያደርግ እንጂ ችግሩን የሚቀርፍ እርምጃ አይደለም፡፡ ነባሩ የኦህዴድ አመራር፣ ህወሓት፣ ሌሎች ነባር አመራሮች ወይም ታጋይ ጀነራሎች ለምን ሲባል በእንደዚህ ዓይነት የጥፋት መንገድ ሊሰለፉ እንደሚችሉ "የሚያውቀውi" የሴራ ፖለቲካ አራማጁ ሀይል ብቻ ነው፡፡ የሴራ ፖለቲካ ከኢትዮጵያ አገሬ ምድር ጠፍቶ የማይበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ተስፋ አለኝ፡፡ አበቃሁ፡፡

ሰላሙን ያብዛላቹ!

**መስከረም 2010 ዓ.ም.**

**መታሰቢያ መ.**